የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር
(ኢብአግ)

ETHIOPIAN NATIONAL UNITED FRONT
(ENUF)

# ከኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር ሠራዊት ማዕከላዊ "ዓለት" ቢሮ
# የተላለፈ አስቸኳይ ኢትዮጵያዊነት ጥሪ

ቁጥር ዓለት/ዘ/መ/002/97
ግንቦት 30 ቀን 1997 ዓ.ም.

ለመላው ኢትዮጵያ ከአጥናፍ
እስከ አጥናፍ ያላችሁ የአንድነት
አርበኞች በሙሉ

በያላችሁበት፣

ታላቁና አርቆ አስተዋዩ ሕዝባችን፣ ሥነ ምግባሩ የሚያስደንቅና የሚያስገርም ቢሆንም፣ በስህተተኛውና አዕምሮ በጎደለው ወያኔ/ኢሕአዴግ የተሰጠው ጊዜ ከበቂ በላይ በመሆኑ፣ የባለጌ ባለሟል እንዲሉ እያበለሻሸ ነውና ይበቃል።

ደነዝና አርቆ የማይመለከት የጠቅላይ ሚኒስትራችን ካቢኔ በሕዝባችንና በልጆቻችን ላይ በ25/09/97 ያደረሰው በደል ትዕግስታችንን እንድናሟጥጥና በሰለጠነ ሕዝብ አካሄድ ያደረግነውን እንድናፈርሰው እየገፋፋን ስለሆነ፣ የሕዝባችንን ፈቃድ እየጠየቅን ለምንወስደው ምላሽ አሁንም ወያኔ/ኢሕአዴግ ቆም ብሎ እንዲያገናዝብ እንጠይቃለን። ስለዚህ የምናፈቅርህና የምንወድህ ወገናችን ኢትዮጵያዊ ሁሉ፣ የልጆቻችን ደም ፈሶ ዝም ልንል አላስቻለንም። ሀዘናችን መሪር ነው። ይህን የሚረዳ በደሉ የደረሰበት ብቻ ነው። ልቡ የደነዘና ዐይኑ የታወረ ወያኔ/ኢሕአዴግ፣ ሥልጣኑን መከታ በማድረግ አሁንም እያቅራራ ነው። እፍረትና በደሉ ለእርሱ አልተሰማውም።

ስለዚህ እሚያቆስል ቆስሎ እንዲያየው ያስፈልጋል። በመሆኑም ጠንከር ያለ፣ የተባበረ እርምጃ እንድንወስድ ያስገደደን ስለሆነ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተቃዋሚ ኃይሎችን በመደገፍ በጣት የሚቆጠሩትን አጥፊ ቡድን አባላትን (1) መለስ ዜናዊ (2) አዲሱ ለገሠ (3) በረከት ስምዖን (4) ተፈራ ዋልዋ (5) ስብሀት ነጋ (6) አባይ ፀሐዬ (7) እንድርያስ እሸቴ (8) ሥዩም መስፍን (9) አባዱላ ገመዳ (10) ጂነዲን ሳዶ (11) የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽነር ወርቅነህ፣

እነዚህን የሕዝብ እውነተኛ ጠላቶች፣ እጃቸው በደም የተበከለና የረከሰ፣ በተጨማሪም በዚህ ሁሉ ግፍ አጋፋሪ የሆኑትን አባ ጳውሎስን የሕዝብ ልጅ የሆናችሁት የመከላከያ ሠራዊት፣ የፖሊስ ሠራዊት፣ የደህንነት ጥበቃ አባላትና የአገሪቱ ተጠባባቂ ኃይል በሙሉ፣ በደል አድራጊዎቹን በቁጥጥር ሥር በማዋል፣ ለሕዝብ ፍርድ እንድታቀርቡ በሰከነ መልኩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር የሠላም አስከባሪ ሠራዊት ማዕከላዊ "ዓለት" ቢሮና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የመጨረሻውን ሥርዓት ደንብ ባለው መልኩ እየጠየቁ፣ ይህ ሁኔታ በተረጋጋ መልክ ቢከናወንና ሥርዓትና ደንብን በተከተለ አካሄድ ቢሄድ መላው ዓለም ለሕዝባችን የሰጠውን ከበሬታና አድናቆት የበለጠ የሚያጎላው ነው።

ይህም ኢትዮጵያን ከጥፋት ማዳን በመሆኑ፣ እኛም የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር ሠላም አስከባሪ ሠራዊት ማዕከላዊ "ዓለት" ቢሮ የአጋራችንን በጎ የተግባር ምላሽ በመረጋጋት እየተጠባበቅን፣ መላው የኢትዮጵያን ሕዝብንም ትግልህ በተናጠል ሳይሆን በተቀነባበረ፣ በበሳል አመራርና ሥልት የተደረገ መሆን ስላለበት፣ የምትነሣበት ትክክለኛው ጊዜና ወቅቱ ይገለጽልሀል። እስከዛው በያለህበት ተዘጋጅተህ ተጠባበቅ።

በጥበብና በረቀቀ ሥልት የተመራ
እንቅስቃሴ ግቡን በትክክል ይመታል።